

# በጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች ላይ የእይታ እና የመስማት ስጋቶችን መፍታት፡-

# Washington ግዛት የሚሆን ባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ Thee-Pronged Approach(ባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ)

## *Early Support for Infants and Toddlers(ከቅድመ ድጋፎች ለህፃናት እና ታዳጊዎች) (ESIT) ፕሮግራም የተገኘ መግቢያ*

የዋሽንግተን ሴንሰርሪ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎቶች Washington Sensory Disability Services (የዋሽንግተን ሴንሳሪ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎቶች) (WSDS) በሙያዊ እውቅና ያላቸውን መስፈርቶች በመጠቀም ፣ Three-Pronged Approach(ባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ) (TPA) የወላጆችን ስጋቶች፣ የሚታዩ የጨቅላ ሕጻናት ባህሪያትን እና ከመስማት እና የማየት ችሎታ ጋር የተያያዙ የዕድገት ችሎታዎችን ለመመዝገብ እንደ መሳርያ አድርጎ ዲዛይን አድርጓል።

የዚህ መሳሪያ ዓላማ ለሶስት ይከፈላል፡-

1. የESIT አቅራቢዎች የልጁን እይታ እና/ወይም የመስማት ችሎታ ሊነኩ የሚችሉ የአደጋ መንስኤዎችን መረዳትን ማሻሻል።
2. የሕፃኑ የመስማት እና የማየት ችግር እንደተቀረፈ ወይም "እንደተጣራ" ማስረጃ ለማቅረብ።
3. የሕፃኑ የመስማት እና/ወይም የማየት ችሎታ ተጨማሪ የምርመራ ግምገማን መቼ እንደሚያረጋግጥ ለመወሰን።

ዋናው ዓላማው በልጆች እድገት ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ለመቀነስ በተቻለ ፍጥነት የመስማት እና የእይታ ስጋቶችን ለመለየት ነው።

Three-Pronged Approach(ባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ) ተጨባጭ የማጣሪያ ሂደቶችን ለመተካት የታለመ አይደለም። በሐሳብ ደረጃ ፣ ከኦቶአኮስቲክ ልቀቶች (OAE) የመስማት፣ የእይታ ፎቶግራፍ እና/ወይም የምርመራ ግምገማ ጋር በሕጻናት ኦዲዮሎጂስት ፣ የዓይን ሐኪም ወይም ኦፕታልሞሎጂስት ምርመራ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ ፣ ነገር ግን፣ እነዚህን የስሜት ህዋሳት አካባቢዎች እና የመስማት እና የማየትን መረጃ በአንድ ቦታ ለመመዝገብ ለESIT አቅራቢዎች ያለው ብቸኛው ዘዴ TPA ነው።

ESIT ስለ የመስማት እና የማየት ወቅታዊ መረጃ በእያንዳንዱ ልጅ Individualized Family Service Plan(የግለሰብ ቤተሰብ አገልግሎት እቅድ) (IFSP) ውስጥ እንዲካተት ይፈልጋል። TPA በልዩ ሁኔታ የተነደፈው ለESIT ነው እና መረጃውን እንደ ቤተሰብ የመቀበል ሂደት አካል ሆኖ እንዲሁም ከዚያ በኋላ በየዓመቱ በIFSP ውስጥ ከተመዘገበው ውጤት ጋር ለመያዝ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

---

*የዚህን ሰነድ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ ፣ እባክዎን DCYF Constituent Relations(የDCYF አባል ግንኙነቶች)ን በ (1-800-723-4831 | 360-902-8060 ፣ **ConstRelations@dcyf.wa.gov**) ያነጋግሩ።*

DCYF PUBLICATION FS_0069 AM (11-2021) Amharic

Washington State Department of CHILDREN, YOUTH & FAMILIES